# ሳሙዔል ዓለማየሁ--የሕያው ታሪክ ባለቤት

የኢሕአፓ አንዱ መለያው በጋራ አመራር ማመኑና በገቢርም ይህንን በስራ በማዋሉ ነው:: አልፎ አልፎ ግን ከስንዴ መሀል እንክርዳዱ አይጠፋምና አንዳንዶች ተኪ የለንም፤ ተክለ ሰብ ገንብተና ልና እኛ ያልነው ካልሆነ ወዮለት ድርጅቱ በማለት ለራሳቸው ብቸኛና ከፍተኛ ቦታን ሰጥተው ድርጅቱን ተፈታትነውታል። ግን ተኪ መሙላቱንና ድርጅቱና አባላቱ ለአንጃ ወይ ግብዞች ቦታና ትዕግስት እንደሌላቸው ደግሞ ሊቀመንበር በሉን/እንሁን ያሉት ሁሉ መማር ተገደዋል።

ያም ሆኖ ግን ከድርጅቱ ሲለዩ በከፍተኛ ደረጃ የሚያጎሉ ፤ አይ በነበሩ የምንላቸው ጓዶች ነበሩ፡ የዛሬ ሶስት ዓመት የተለየን ሳሙዔል ዓለማየሁ ይህን ዓይነት ጓድ ነበር። ተኪ የለኝም ባይ ስላልነ በርና ትሁትም ስለነበር ጉዳቱ ይበልጥ ጓዶችንም ድርጅቱንም ነክቷል። ሳሙዔል በሠራተኛው ማህበር ብዙ የታገለ ሲሆን ወደ ኢሕአፓ ደግሞ የመጣው ገና በአሜሪካ በትምህርት ላይ ሳለ ከእነ እሸቱ ጮሌና ሌሎችም ጋር ነበር። ወደ አዲስ አበባ ተመልሶ በሠራተኛው ማህብራት ዙሪያ ሲሰራም ቆይቶ የደርግ አፈና ሲጠናከር ተይዞ ሲለቀቅ መስሪያ ቤቱን ለቆ ተስውሯል። ከዚያም ለረጅም ዓመታት በአዲስ አበባ፤ሐረር፤ ወሎ ወዘተ በድርጅታዊ ስራ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርጓል።በአሲምባና ጎንደርም የትጥቅ ትግሉ እንቅስቃሴ፤ በሱዳን መዋቅር ወዘተም ሲሰራ ቆይቷል። በድንገት እስኪለየን ድረስም በኢሕአፓ በአመራርና ከዚያም በሌሎች እርከኖች ሲታገ ል ቆይቷል። ሳሙዔል ዓለማየሁ ፀንቶ መታገሉ ታሪኩ ሲሆን ልዩ ያደረገው ደግሞ የድርጅት ስራ ችሎታው ብቻ ሳይሆን ቀደም ሲል እንደተገለጠው እዩኝ እወቁኝ ባይ አለመሆኑና ከጓዶች ጋር የነበረው ግሩም ግንኙነት፤እርጋታና የመቻል ጠባዩ ነበር። ዛሬ ያ ቀልዱና በነበረበት ቦታ የሚስተጋባው ሳቁ ትዝ የሚለን ሁሉ በተለይ እሱ ዛሬ በነበር ብለን የምንለው ወሳኝ ከሆነው የድርጅት ስራ አንፃር፤ ድርጅቱን ከተጋረጠበት አደጋዎች ከመከላከል አንፃርና የጓዶችንም ውህደትና ፅናት ከመገንባት አንፃር ሊያደርግ ይችል የነበረውን አስተዋፅዖ በማሰብ ነው:: ሳሙዔል በጣም ትግስተኛና ሰውን አክባሪ ነበር--ግን ለፀረ ሕዝቦች ደግሞ ትግስትም ቦታም አልነበረውም። ቻይ ነበር ግን ድርጅትና ሕዝብ ላይ ለሚመጣ ጥቃት ደግሞ ትከሻውን የሚሰጥ አልነበረም። ተገቢውን ስራና ከዚያም በላይ እየሰራ በአንፃሩ ግን እወቁልኝ የሚል መንፈስም ስሜትም አልነበረወም። አደገኛ ተልዕኮዎችን ሁሉ ተወጥቷል። ፅኑ አቅዋም ነበረው፤ በውይይት ና በመግባባት አማኝ እንጂ ንዴትና ቁጣን አስቀዳሚ አልነበረም።ችሎታ የነበረውና የተማረ ጓድ የነበረ ቢሆንም አልተማረም፤አላወቀም በሚል ማንንም የሚንቅ ሰው አልነበረም። ሳሙዔል ታሪኩን ቅንጣት ሳያበላሽና ሳያቆሽሽ ኢሕአፓ እንደሆነና እንደነበር አልፏል።

ሳሙዔል የሕያው ታሪክ ባለቤት ነው። ቤተሰቡም ኢሕአፓም ይኮሩበታል። አርአያነቱም ቀጣይ ነው። ቢኖርልን ኖሮ ምንኛ ደስ ባለን፤ ምንኛ በጠቀመን ነበር። ከዚህ ባሻገር ግን ለእኛ ትዝታው በሕይወት ሳለ የሰራው፤ የታገለውና ምሳሌ ሆኖ ብዙዎችን ያስተማረው ነው። ኢሕአፓነቱ ነው:: እንዳከበርነውና እንዳስከበረን አልፏል። ታሪኩ ግን ሕያው ሆኖ አብሮን ይቀጥላል።

ኢያሱ ዓለማየሁ